# PCR VS. ፈጣን የቤት አንቲጅን ምርመራዎች

## መመሪያ

የኮቪድ-19 ኬዞች እየጨመሩ ሲሄዱ ማንኛውም ምርመራ ምንም ካለማድረግ የተሻለ ነው።
አማራጮች ካሉዎት በእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ ያሉትን ምክሮች ይከተሉ።

**ወደ አንድ የቤት ውስጥ ወይም ሰዉ የበዛበት ፕሮግራም እየሄዱ ነው?**
ፈጣን የቤት ዉስጥ ምርመራ በተመሳሳይ ቀን (ከፕሮግራሙ በፊት) የተሻለ ነው።

**የኮቪድ-19 ኖሮበት ነገር ግን ምልክቶች ከሌሉት ሰው ጋር ተቀራርበዋል?**
PCR ይመረጣል፣ ነገር ግን ፈጣን የቤት ዉስጥ ምርመራ ጥሩ ነው። ከተጋለጡ በኋላ ከመመርመሩዎ በፊት 5 ቀናት ይጠብቁ።

**በአውሮፕላን ሊጓዙ ነው?**
የጊዜ እና የምርመራ አይነት በአየር መንገዱ መስፈርቶች ላይ የተመሰረተ ነው፣ ነገር ግን የ PCR ምርመራዎች ጉዞ ከ 3 ቀናት ያልበለጠ ጊዜ ውስጥ ቢሆን ይመረጣል።

**ሰዉ ወደ በዛበት / የቤት ውስጥ ፕሮግራም ወይም ሌላ ከፍተኛ የአደጋ ሁኔታ ሄደዋል?**
ክስተቱ ከተፈጸመ ከ 5 ቀናት በኋላ ፈጣን የቤት ዉስጥ ምርመራ ወይም PCR ምርመራ ያድርጉ።

**የኮቪድ-19 ምልክቶች አሉቦት እና እርስዎ የቅርብ ግንኙነት ነበርዎት?**
የ PCR ምርመራ በጣም ጥሩ ነው፣ ነገር ግን ፈጣን የቤት ውስጥ ምርመራ ጥሩ ነው፣ ምልክቶቹ እንደጀመሩ ወዲያውኑ ይውሰዱ።

**የኮቪድ-19 ምልክቶች ኖርት ግን የቅርብ ንክኪ አልነበርዎትም?**
የ PCR ምርመራ በጣም ጥሩ ነው፣ ነገር ግን ፈጣን የቤት ውስጥ ምርመራም ጥሩ ነው፣ምልክቶቹ እንደጀመሩ ወዲያውኑ ይውሰዱ።

## የምርመራ ውጤቶችን መረዳት:-

- ***ፖዘቲቭ ፈጣን የቤት ዉስጥ ወይም PCR ምርመራ*** ውጤት ማለት ቫይረሱ አለብዎት ማለት ነው። ከታመሙ እና ከሌሎች የሚርቁ ከሆነ ምን ማድረግ እንዳለብዎት የአሌክሳንድሪያ ጤና ዲፓርትመንት (ADH) መመሪያን ይከተሉ። ምርመራዎት ፖዘቲቭ ከሆነ በኋላ በትክክል ምን ማድረግ እንዳለብዎት ለማወቅ ወደ alexandriava.gov/COVIDNextSteps ይሂዱ።
- ***ኔጌቲቭ ፈጣን የቤት ዉስጥ ምርመራ*** ውጤት ማለት ምርመራው ቫይረሱን አላገኘውም እና ኢንፌክሽን ላይኖርብዎት ይችላል ነገር ግን ሙሉ በሙሉ አያስወግደውም። የኮቪድ-19 ኢንፌክሽንን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ቢያንስ ከ24 ሰዓታት በኋላ ሌላ ምርመራ ማድረግ አለብዎት።
- ***ኔጌቲቭ ፈጣን የቤት ምርመራ እና የትኛውም ዓይነት ፖዘቲቭ ምርመራ ካጋጠመዎት፣ የመጀመሪያ ምርመራዎ ትክክል ያልሆነ*** ወይም ከተጋለጡ በኋላ በጣም ፈጥኖ የተወሰደ ሊሆን ይችላል፣ እና እርስዎ ፖዘቲቭ እንደሆኑ መገመት አለብዎት።

### ፖዘቲቭ ፈጣን የቤት ምርመራ? እኛ ልንረዳዎ እንችላለን!

የአሌክሳንድሪያ ጤና ዲፓርትመንት በደህንነት ቤት ለመቆየት ተጨማሪ መረጃ እና ግብዓቶችን እንዲሰጥዎ አጭር ቅጽ ይሙሉ:- **redcap.link/aiv7nppx**